አማራ ባንክ አ ■ ማ ■ (በምስረታ ላይ ያለ)

ለትውልደ ኢትዮጵያን የውጭ ሀገር ዜጎች የአማራ ባንክ አ.ማ. የአክስዮን ሽያጭ መግለጫ።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የካቲት 2012 ዓ.ም

1ስረታን5TPackards dividends nor for the produces of the l and void, but liabilities arising thereunder onvertable አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የካቲት 2012 ዓ.ም

ለትውልደ ኢትዮጵያን የውጭ ሀገር ዜጎች የአማራ ባንክ አ.ማ. የአክስዮን ሽያጭ መግለጫ።

ግዙፉ የግል ባንክ በመሆን ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ የሚገኘው አማራ ባንክ፣ ለትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጎች አክስዮን ለመሸጥ የሚያስችለውን የብሄራዊ ባንክ መመሪያ መውጣት በመጠባበቅ የአክስዮን ሽያጭ ጊዜውን እስከ የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም በማራዘም የመመሪያውን መውጣት ሲጠባበቅ የቆየ ሲሆን፣ መመሪያው የካቲት 20 ቀን 2012 ዓ.ም ወደስራ መግባቱን ተከትሎ፣ ከዲያስፖራ ማህበራት እና ከትውልደ ኢትዮጵያውን የውጭ ሀገር ዜጎች የአክስዮን ሽያጭ ጊዜ ገደብ እንዲራዘም የቀረበውን መጠነ ሰፊ ጥያቄ በመቀበል፣ የአክስዮን ሽያጭ ጊዜውን እስከ ሚያዚያ 07 ቀን በማራዘም ጠቅላላ ጉባኤውን ሚያዚያ 24 ቀን 2012 ዓ.ም ለማከናወን ውሳኔ ላይ ተደርሷል። በምስረታ ላይ የሚገኘው አማራ ባንክ የአክስዮን ሽያጭ ከጀመረበት ነሃሴ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ፦

- ከብር 5,300,000,000.00 (አምስት ቢሊየን ሶስት መቶ ሚሊየን ብር) በላይ የተፈረመ (subscribed) አክስዮን፤
- ከብር 4,000,000,000.00 (አራት ቢሊየን ብር) በላይ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ካፒታል (paid up) አክስዮን የሸጠ ሲሆን፣ የአክስዮን ሽያጩ እስከ ሚያዚያ 07 ቀን ድረስ ቀጥሏል።

ጳጉሜ 3 ቀን 2011 ዓ.ም ወደ ስራ በገባው የባንክ ስራ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1159/2011 መሰረት የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያውን ባለቤትነት የተቋቋሙ ኩባንያዎች ወይም በኢትዮጵያውን እና በትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ሀገር ዜጎች በጋራ የተቋቋሙ ኩባንያዎች የባንኩን አክስዮን ለመግዛት መብት አላቸው። በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ ስራ ላይ በመዋሉ፣ አማራ ባንክ ለትውልደ ኢትዮጵያውያን /ዲያስፖራ/ አክስዮን ለመሸጥ የሚያስችለውን ዝግጅት አጠናቋል።

1. *የአክስዮን ግዥው እንዴት ይፈጸማል?*

- ከስር በሰንጠረዥ ተ.ቁ 2 ላይ ከተመለከቱት ባንኮች አንዱን ባንክ በመምረጥ ለመግዛት የወሰኑትን የአክስዮን መጠን በጠቅላላ ወይም ሃምሳ በመቶ (50%) በአማራ ባንክ አ.ማ ዝግ ሂሳብ ውስጥ ማስገባት፤
- ከዝግ ሂሳቡ በትዩዩ ከተቀመጠው የአማራ ባንክ አ.ማ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ ቃል የተገባውን (የተፈረመውን) ወይም ሙሉ ክፍያ የሚፈጸም በሆነ ጊዜ የጠቅላላውን ክፍያ 5% (አምስት በመቶ) የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤[1]
- የተፈጸመው ግዥ ሃምሳ በመቶ (50%) በሆነ ጊዜ፣ ቀሪ ክፍያውን ሃምሳ በመቶ (50%) ባንኩ ስራ ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መክፈል፤

[1] የአክስዮን ግዥው ክፍያ ተፈጽሞ የአገልግሎት ክፍያው ሳይፈጸም ቢቀር የአክስዮን ግዥው እንዳልተፈጸመ ተቆጥሮ ግዥው ያለመመዝገብ ውጤት ያስከትላል።

- አክስዮን የገዛችው/የገዛው ሰው ገንዘቡን ከላይ በተመለከተው መልኩ ገቢ ካደረገች/ካደረገ በኋላ፣ ግዥው ነዋሪነቱ ከኢትዮጵያ ውጭ በሆነ ጊዜ፣ ነዋሪነቷ/ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የግዥዋ/ው ህጋዊ ወኪል የውክልና ኮፒ እና መታወቂያ (የቀበሌ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት)፣ ገንዘቡ ገቢ የተደረገባቸውን የባንክ ደረሰኞች ኮፒ፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቹህን የሚያረጋግጥ የመታወቂያ ካርድ /ቢጫ ካርድ/ ፎቶ ኮፒ እና የግዥዋ/ውን ፓስፖርት ኮፒ በመያዝ ገንዘቡ ገቢ በተደረገበት ባንክ በአንዱ ቅርናጫፍ ወይም በአዲስ አበባ ከተማ ካዛንችስ አካባቢ በሚገኘው በአማራ ባንክ አ.ማ የፕሮጀክት ጽ/ቤት ብሉምቴክ ህንጻ 2 ኛ ፎቅ ላይ (በጁፒተር እና በኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል መሀከል በሚገኘው) በመቅረብ የአክስዮን ሽያጩን ቅጽ መሙላት እና መፈረም ይኖርባታል/ይኖርበታል።

2. ሌላስ ምን ግዴታ አለ?

ከላይ ከተገለጸው ቅድመ ሁኔታ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር 73/2020 መሰረት ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ሀገር ዜጎች የአክስዮን ግዥውን የምትፈጽሙት፦

1 ኛ. በአሜሪካን ዶላር፣ በእንግሊዝ ፓውንድ፣ በዩሮ እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተቀባይነት አላቸው ብሎ በሚያሳውቃቸው የሌሎች ሀገራት ገንዘብ ነው፤

2 ኛ. ክፍያውን መፈጸም የምትችሉት ከምትኖሩበት ሀገር በባንክ በኩል ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ካላቹህ የዲያስፖራ አካውንት /from non-residence foreign account/ በማዘዋወር ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ ምንዛሬ የትርፍ ክፍፍል ማግኝት ከምትችሉበት ኢንቨስትመንት ከምታገኙት ትርፍ ላይ በባንክ በኩል ከሚተላለፍ ክፍያ ብቻ ነው፤

3 ኛ. የባንክ ደረሰኝ /credit advice/ ማቅረብ ግዴታ ነው፤ ደረሰኙ የአክስዮን ግዥውን ማንነት፣ የገንዘቡን መጠን እና የክፍያውን ምክንያት መግለጽ አለበት፤

4 ኛ. በአዋጅ ቁጥር 270/1994 መሰረት ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቹህን የሚያረጋግጥ የመታወቂያ ካርድ /ቢጫ ካርድ/ ማቅረብ የምትችሉ መሆን አለበት።

3. ምን ያህል አክስዮን መግዛት ይቻላል?

- የአንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 1,000.00 (አንድ ሽህ ብር) **[$ 30.3874 (**ሰላሳ ዶላር ከ **3874** ሳንቲም**)]**፤
- መግዛት የሚቻለው ዝቅተኛ የአክሲዮን ብዛት **10 (**አስር**)** ወይም ብር **10,000.00 (**አሰር ሽህ ብር**) [$ 303.874 (**ሶስት መቶ ሶስት ዶላር ከ **874** ሳንቲም**)]**፤
- አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት መግዛት የሚችለው ከፍተኛ የአክሲዮን መጠን ብዛት **100,000 (**አንድ መቶ ሽህ አክስዮን**)** ወይም ብር **100,000,000 (**አንድ መቶ ሚሊዮን ብር**) [$ 3,038,740 (**ሶስት ሚሊየን ሰላሳ ስምንት ሽህ ሰባት መቶ አርባ ዶላር**)]**፤

ሰንጠረዥ 1፡ የአክስዮን ሽያጭ በብር እና በተለያዩ ሀገራት ገንዘብ[2]

	አክስዮን	በብር	በዶላር	በዩሮ	በፓውንድ
የአንዱ አክስዮን ዋጋ	**1**	**1,000.00**	**$ 30.6883**	**28.2243**	**24.8487**
የተፈቀደ ዝቅተኛ ግዥ	**10**	**10,000.00**	**$ 306.883**	**282.243**	**248.487**
የተፈቀደ ከፍተኛ ግዥ	**100,000**	**100,000,000.00**	**$ 3,068,830.00**	**2,822,430.00**	**2,484,870.00**

4. አንዳንድ መረጃዎች ስለ አክስዮን ሽያጭ

1. በባንክ ስራ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1159/2011 አንቀጽ 9 መሰረት ትውልደ ኢትዮጵያውያን የውጭ ሀገር ዜጎች አክስዮን ግዥ የሚፈጽሙት በውጭ ምንዛሬ ብቻ ሲሆን፣ ከትርፍ ክፍፍልም ሆነ ከአክስዮን ሽያጭ የሚገኝውን የገንዘብ ክፍያ መውሰድ የሚችሉት በኢትዮጵያ ብር ብቻ ይሆናል። /No Repatriation Right neither for the dividends nor for the produces of the sale of the shares./

2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከትርፍ ክፍፍል የሚገኝውን ገንዘብ በዚያው ባንክ ለተፈረመው አክስዮን ክፍያ ለማዋል ወይም ባንኩ ለሚያወጣቸው አዳዲስ አክስዮኖች ግዥ ለመፈጸም መጠቀም የተፈቀደ ነው።

3. በውጭ ምንዛሬ ከሚገኝው ሽያጭ ውስጥ 30% (ሰላሳ እጅ) የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሚያወጣው የዕለቱ አማካኝ የግብይት ዋጋ /Mid Exchange Rate/ በኢትዮጵያ ብር በመክፈል የውጭ ምንዛሬውን ለመጠቀም ስልጣን ያለው ሲሆን፣ ቀሪውን 70% (ሰባ እጅ) በምስረታ ላይ ያለው አማራ ባንክ ከብሄራዊ ባንክ የስራ ፈቃድ እንዳገኝ የሚተላለፍለት እና በባለቤትነት የሚገለግልበት ይሆናል።

4. በየትኛውም ዓለም የሚኖሩ ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሰዎች የአክስዮን ግዥ ክፍያውን የኢትዮጵያን ብር ጨምሮ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው ማናቸውም የውጭ ምንዛሬ መክፈል የሚችሉ ሲሆን፣ በውጭ ምንዛሬ ብቻ ለመክፈል የሚገደዱት ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጎች ብቻ ናቸው።

5. የባንኩን አክስዮን በኢትዮጵያ ብር ከፈረሙ በኋላ ዜግነታቸውን ለሚቀይሩ ኢትዮጵያውያን በብር የፈረሙት የአክስዮን ግዥ እና ቀሪውን ክፍያ በኢትዮጵያ ብር ለመክፈል የሚፈቀድላቸው ሆኖ ግዥው ለሁልጊዜውም

[2] የአክስዮኑ ዋጋ በተለያዩ ሀገራት ምንዛሬ የተቀየረው ከብሄራዊ ባንክ ድረገጽ እ.ኤ.አ በቀን 2020-02-27 በወጣው አማካኝ የግብይት ዋጋ /Mid Exchange Rate/ (የአንዱ $ ዋጋ = ብር 32.5858፣ የአንዱ ዩሮ ዋጋ = ብር 35.4305፣ እና የአንዱ ፓውንድ ዋጋ = ብር 40.2437 መሆኑን መሰረት በማድረግ ነው።

ክፍያው በሚፈጸምበት ቀን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚያወጣው የመግዣ እና የመሸጫ አማካኝ የውጭ ምንዛሬው ዋጋ /Mid Exchange Rate/ የአክስዮን ግዥው የሚፈጸምበት ዋጋ ነው።

የሚጸናላቸው ሲሆን፤ ዜግነታቸውን ከቀየሩ በኋላ የሚፈጽሚቸው አዲስ የአክስዮን ግዥ ክፍያ የሚፈጸመው በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ምንዛሬዎች ብቻ ይሆናል።

6. የባንኩን አክስዮን ከኢትዮጵያዊውያን ለትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጎች በሽያጭ ማስተላለፍ ይቻላሉ፤ ሽያጩ የሚከናወነው ተቀባይነት ባለው የውጭ ምንዛሬ ሁኖ ክፍያው መፈጸም ያለበት በባንክ በኩል ነው፣ ሆኖም የአንዱ አክስዮን የሽያጭ ዋጋ ከመደበኛው የአንዱ አክስዮን ዋጋ ሊያንስ አይችልም።

7. ኢትዮጵያውን ባለአክስዮኖች ለትውልደ ኢትዮጵያውን የውጭ ሀገር ዜጎች አክስዮኖችን በስጦታ ማስተላለፍ አይችሉም፣ በውርስ ግን ሊተላለፉ ይችላሉ።

8. በኢትዮጵውን እና በትውልደ ኢትዮጵያውና በጋራ ባለቤትነት የተያዙ ኩባንዎች የሚፈጽሚቸው የአክስዮን ግዥዎች፣ ክፍያው የሚፈጸመው የኩባንያው ባለድርሻዎች ባላቸው የድርሻ ልክ በውጭ ምንዛሬ እና በኢትዮጵያ ብር ነው።

ሰንጠረዥ 2፡ የባንኮች ስም፣ ስዊፍት ኮድ እና የሂሣብ ቁጥር።

ተ/ቁ	ባንክ	ስዊፍት ኮድ	የዝግ ሂሳብ ቁጥር የአክስዮን ግዥ ክፍያ **(Subscription Payment AC)**	የአገልግሎት ክፍያ ሂሣብ ቁጥር **(Service Charge AC)**
1.	ዳሽን ባንክ	**DASHETAA**	**1414173495012**	**1414174146012**
2.	አቢሲንያ ባንክ	**ABYSETAA**	**29572763**	30053303
3.	የኢ/ንግድ ባንክ	CBETETAA	**1000324555068**	**1000324748044**
4.	አዋሽ ባንክ	AWINETAA	02307245885500	02307245885501

እስከ ሚያዚያ 07 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ አክስዮን ለሚገዙ የመስራችነት መብት የተጠበቀ ነው። ለበለጠ መረጃ፣ ማብራሪያ እና የአክስዮን ሽያጩን በተመለከተ ድጋፍ ለማግኘት በሚከተሉት የስልክ እና የኤሌክትሮኒክ አድራሻዎቻችን ያግኙን፣ ያናግሩን።

ማስታወሻ፡ የአክስዮን ሽያጭ ፎርም በድረገጻችን http://www.amharabank.com.et/ ይገኛል።

አድራሻዎቻችን	ስ/ቁጥሮች	0911 24 81 60 0912 00 18 19 0941 46 66 07	0911 62 13 30 0911 13 30 14 0911 65 35 09
	Email:	Info@amharabank.com.et	
	Facebook	http://facebook.com/officialamharabank	
	Twitter	http://twitter.com/amharabank	
ቢሯችን፦ አዲስ አበባ፣ ካዛንቺስ (በጁፒተር እና በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል መሃከል በሚገኘው) ብሉም ቴክ ህንጻ 2 ኛ ፎቅ ነው።			

አማራ ባንክ አ.ማ. (በምስረታ ላይ)